# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

በዓለ ጰራቅሊጦስ (ጰንጠቆስጤ) ስምንተኛው ሰንበት

ዘመነ ጰራቅሊጦስ የሚባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ ከሃምሳኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ ፲፮ ቀን ድረስ ያለው ነው። በእነዚህ ሳምንታትና ዕለታት የሚዘመረው መዝሙር የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ትንሣኤን ዕርገትን የሚያነሣ ይሆናል።

## የዕለቱ ምስባክ

ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር
ንትፌሳህ ወንትሐሰይ ባቲ
ኦ እግዚኦ አድህንሶ

ይህች ዕለት እግዚአብሔር ሥራውን
የሠራባት ዕለት ናት
እንደሰት በስዋም ሐሴት እናድርግባት
አቤቱ አሁን አድን

መዝ ፩፻፲፯፥፳፬

ወንጌል፥ ዮሐ ፳፥፩-፲፱
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይትፌሳህ ሰማይ ወትትሐሰይ ምድር
«ሰማይ ይደሰታል ምድርም ሐሴት ታደርጋለች»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፩-፳ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፩፥፩-፲፫ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፪፥፳፪-፳፯ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

# የዕለቱ ትምህርት

## መንፈስ ቅዱስ ማነው?

***መንፈስ ቅዱስ ፈጣሬ ዓለማት ገባሬ ሰማያት ነው።***

ይህንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ «ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ ... የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» ይላል (ዘፍ ፩፥፪)። የዓለም ሁኔታ ሳይጸና ምድር እንደውሃ በምትዋልልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያዘጋጃት ነበር። ባልጸናችው ምድር ላይ የመንፈስ ቅዱስ መንሳፈፍ በአንዲት የበረሃ ወፍ ታቅፎ ያልረጋው እንቁላል ረግቶ ጫጩት እንደሚሆን እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በባህር ላይ በመስፈፍ ያልጸናውን ዓለም እንዲጸና አድርጎታል። ዘማሪውም «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም በአፉ እስትንፋስ» (መዝ ፴፪፥፮) በማለት የምድርና የሰማይ ሠራዊት በአካላዊ እስትንፋስ እንደጸኑ ይነግረናል። ኢዮብም በበኩሉ «የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ» (ኢዮ ፴፫፥፬) በማለት በአካላዊ እስትንፋስ አብ ወወልድ በባሕርያዊ ሕይወተ አብ ወወልድ ሕይወትን ሰው ሁሉ እንደለበሰ ይነግረናል። ይህም እውነታ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» (ዘፍ ፪፥፯) ተብሎ ከተጻፈው ጋር ይስማማል። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር በአንዲት መለኮታዊ ክሂል ዓለምን ያሆነ፣ ያደረገ፣ የፈጠረ፣ ፈጣሪ፣ ገባሪ፣ ሕያው ጌታ ነው።

> መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር ዕሪየ መለኮት በመሆኑ አግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ይባላል እግዚአብሔር ስሙ ነው።

***መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር ዕሪየ መለኮት በመሆኑ አግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ይባላል እግዚአብሔር ስሙ ነው።*** መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር በማለት ከአብ ከወልድ ጋር ያለውን ዕሪናዊ፣ እግዚእናዊ፣ ዕሩየ መለኮትነት ይጠቁማል። በትንቢተ አሳይያስ ፮፥፩-፲ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቁልጭ አድርጎ ተርጉሞታል (የሐዋ ሥራ ፳፰፥፳፭-፳፰)። ቅዱስ ጴጥሮስም እግዚአብሔር ብሎ እንደጠራው በሐዋ ሥራ ፭፥፫-፬ ማንበብ እንችላለን።

***ከአብና ከወልድ ጋር ዋህደ መለኮት ዕሩየ መለኮት ቢሆንም ልዩ አካል ነው።***
ለአብ የራሱ የሆነ አካል አለው፤ አብ የሚለው ስሙም ስመ አካል ነው። ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል አብ ይባላል። ወልድም የራሱ የሆነ አካል አለው፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ አካል አለው ከሦስቱ አካል አንዱ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ስመ ግብር ያይደለ ስመ አካል ነው።

ይህንን ትምህርት መጽሐፈ ሕይወት ባሕረ ጥበብ መጽሐፍ ቅዱስ በአጫፋሪ ወይንም በመስተጻምር እንደሚከተለው ይገልጸዋል። «አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» (ኢሳ ፵፰፥፲፮)። ይህ ቃል የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ይገልጻል። ጌታ እግዚአብሔር የተባለው አብ ሲሆን በመስተጻምር መንፈሱ ተብሎ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ነው። ልኮኛል የሚለው ቃለ ትንቢት ደግሞ በሥጋ ማርያም የተገለጸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይጠቁማል። «እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኃነነ ... በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ መጥቶ አዳነን» እንዳለ ሊቁ (የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም) (ማቴ ፳፰፥፲፱)።

***በስሙ ልዩ ነው።***
እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ተለይቶ የሚጠራበት አካላዊ ስሙ መንፈስ ቅዱስ ነው። በመሆኑም ስሙ ልዩ ነው። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። መንፈስ ቅዱስ ስመ አካል ነው። ይህ ስም የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ስም ነው፣ መቼም መች በዚህ ስም አብ እና ወልድ አልተጠሩበትም። ስመ አካለ ወልድ ወልድ ነውና አብ

እና መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትም። አብም የአብ ስም ብቻ ነው የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም በዚህም ስም ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አልተጠሩበትም አይጠሩበትም፤ ስመ አካለ አብ ነውና። ሥላሴ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ግን አካላቸው ስማቸው የተለየ ቢሆንም ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ነው።

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የሚጠሩ የእግዚአብሔር ሦስቱ አስማተ አካላት ግን አይፋለሱም። ይህንን በተመለከተ ሊቁ ቅዱስ አግናጢዎስ የተናገረውን ቃል አንመልከት «አብ ውእቱ አብ ኢኮነ ወልደ ወኢመንፈሰ ቅዱስ፤ ወልድኒ ውእቱ ወልድ ወኢኮነ አብ ወኢመንፈስ ቅዱስ፤ መንፈስ ቅዱስኒ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ኢኮነ አብ ወኢወልደ፤ አብ ኢይፈልስ ለከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢወልድ ለከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢመንፈስ ቅዱስ ለከዊነ አብ ወወልድ።» ትርጉሙ «አብ እርሱ አብ እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለም። ወልድ እርሱ ወልድ እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም እሱ መንፈስ ቅዱስ እንጂ አብ ወይም ወልድ አይደለም። አብ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን አይለወጥም፤ ወልድም አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን አይለጠጥም፤ መንፈስ ቅዱስም አብ ወይም ወልድ ወደመሆን አይለወጥም» በማለት ተነግሮአል (ሃይማኖተ አበው ዘአንጾኪያ ገጽ ፴፯ ክፍል አንድ ቁጥር ፰-፱)። ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ፍጹማንና ሙሉዐን አካላት መሆናቸውን በብቃት ያስገነዘበው ገለጻ አብ ልብ ሲሆን በልብነቱ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ሕሊናቸው በመሆኑ እንደሆነ፤ ወልድም ቃል ሲሆን በቃልነቱ ለአብ እና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ንግግራቸው በመሆኑ እንደሆነ፤ መንፈስ ቅዱስም እስትንፋስ ሲሆን በእስትንፋስነቱ ለአብ እና ለወልድ እስትንፋሳቸው እንደሆነ ወይንም ሕይወታቸው በመሆኑ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን አበውም ሆነ የወሉደ አበው ምእመናን መሠረታዊና ኦርቶዶክሳዊ እምነት ነው።

ሥላሴ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ግን አካላቸው ስማቸው የተለየ ቢሆንም ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ነው።

***ሠራጺ ነው።***

መንፈስ ቅዱስ ቅድመ ዓለም ወልድን ከወለደ አብ ቅድመ ዓለም ስለሠረጸ ሠራጺ ይባላል። ይህም ሠራጺ የተሰኘው ስሙ ከሦስቱ አስማተ አካላት አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ከሦስቱ አስማተ ግብር አንዱ ነው። ሠራጺ የሚለው ስሙም ስመ አካል ስመ ኩነት ያይደለ ስመ ግብር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስመ ግብር ሠራጺ ነው። የወልድ ተወላዲ የአብ ወላዲ አሥራጺ ስመ ግብራቸው እንደሆነ ሁሉ።

መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብ ብቻ ነው። ይህንንም እውነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል። «ወሶበ መጽእ ጰራቅሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ እምኀበ አብ መንፈሰ ጽድቅ ዘይመፅእ እመኀበ አብ ውእቱ ሰማዕትየ። ... እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሠረጸ (የወጣ) መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ስለእኔ ይመሰክራል»(ዮሐ ፲፭፤፳፮)። በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት ፻፶ ሊቃውንትና መሰሎቻቸውም «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት ... ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት አድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ» (ጸሎተ ሃይማኖት ዘኒቅያ) ብለው አቋማቸውን ገልጸዋል።

ኤጲፋንዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቆጵሮስ ደግሞ «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ዘነበበ በኦሪት ወተሰብከ በነቢያት ወነበበ በሐዋርያት ወወረደ በዮርዳኖስ ወኃደረ በቅዱሳን ወከመዝ ነአምን ከመውእቱ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ፍጹም ጰራቅሊጦስ እምአብ ወይወጽእ እምወልድ ዘይነስእ ... በኦሪት በተናገረ፣ በነቢያት በተሰበከ፣ በሐዋርያት ባስተማረ፣ በዮርዳኖስ በወረደ፣ በቅዱሳን ባደረው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ እንደዚሁም ይህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ጰራቅሊጦስ የሚባል ፍጹም መንፈስ እንደሆነና ከአብ የሚመጣ ከወልድ የሚወስድ እንደሆነ እናምናለን» ብሎአል።

***አጽናኝ ነው።***

መንፈስ ቅዱስ አረኛቸውን ላጡት በጎች ሰብሳቢ፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተለይቶ መቆየት ለማይቻላት ቤተ ክርስቲያን አበርታች፤ ሞት፣ ሕመም፣ ኃዘን፣ ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ላጠቃቸው ደቂቀ አዳም አጽናኝ በመሆኑ በግሪክ ጰራቅሊጦስ ይባላል። አማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችንም «እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል (ዮሐ ፲፬፤፲፮)። እንዲሁም «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል» ይላል (ዮሐ ፲፭፤፳፮) በተጨማሪም (ዮሐ ፲፮፤፯-፲፭) ላይ ያለውን ይመልከቱ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

